# የ ASSOCIATION FOR PEACE IN ETHIOPIA/ አሶስዬሽን ፎር ፒስ ኢን ኢትዮጵያ/ APE/

# የበጎ አድራጎት ማህበር

# መተዳደሪያ ደንብ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Authority for Civil Society Organizations

ሐምሌ/2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አንቀጽ 1፡ መቋቋም

የASSOCIATION FOR PEACE IN ETHIOPIA/ አሶስዬሽን ፎር ፒስ ኢን ኢትዮጵያ/APE/ የተባለ ማህበር በሐምሌ ወር 26 ቀን 2014 ዓ.ም ተቋቁሟል፡፡

## አንቀጽ 2፡ ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ASSOCIATION FOR PEACE IN ETHIOPIA/ አሶስዬሽን ፎር ፒስ ኢን እትዮጵያ/ APE/ማህበር በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ "ማህበር" ተብሎ ይጠራል፡፡

## አንቀጽ 3፡ ዓላማ

የማህበሩ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

**ማህበሩ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ /general objective/**

- በሀገራችን ኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላም (sustainable peace) እንዲኖር የሚያስችሉ ሥራዎችን መስራት፡፡

**ዝርዝር ዓላማዎች/specific objectives/:-**

1) ኢትዮጵያውያን ለሰላም እንዲተባበሩ የህዝብ ንቅናቄ ሥራዎችን በመስራት የሰላም ግንባታ/peace building/ ሂደትን ማገዝ፡፡

2) የሰላም ትምህርቶችን/peace education/ እና ሥልጠናዎችን በመስጠት የሰላም አድቮኬሲ/peace advocacy/ ስራዎችን ማስፋፋት፡፡

3) ሲሙሌሽኖችን (Simulations) ፣ ዶክሜንታሪና የሌሎች ሀገራት የግጭት አፈታትና የሰላም ንቅናቄ ተሞክሮዎችን በማቅረብ ሀገር በቀልና ዘመናዊ የግጭት አፈታት/conflict resolution/ ዘዴዎች እንዲበረታቱ መስራት፡፡

4) ጥናቶችን በማድረግ የህዝብን ሰላም ሊያዛቡ የሚችሉ ሁኔታዎችን በመለየት ለቅድመ ጥንቃቄ/early warning/ ሲባል ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ማሳወቅ፣ መፍትሄዎችንም መጠቆም፡፡

5) ማህበራዊና ብሮባንድ ሚዲያዎችን በመጠቀም ሀገራዊ ውይይትና እርቀሰላምን/national dialogue and reconciliation/ የመደገፍ ስረዎችን መስራት፡፡

6) ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ተጋላጭ /vulnerable/ ስለሆኑ ለሰላምና ደህንነታቸው የበለጠ ጥበቃ እና ጥንቃቄ እንድደረግ መስራት፡፡

7) በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲሁም በብሮድባንድ ሚዲያዎች የሚስተዋሉ ህዝብን ከህዝብና ሀይማኖትን ከሀይማኖት ሊያቃቅሩ የሚችሉ ክስተቶች እንዳይስፋፉ መስራት፡፡

8) ንፁሀንን (innocent civilians) ዒላማ ያደረጉ ጥቃቶች እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዲቆሙ መስራት፡፡

9) የሚደረጉ የሰብዓዊ ድጋፎችን/humanitarian support /ማገዝ

## አንቀጽ 4፡ የበጀት ዓመት

የበጎ አድራጎት ማህበሩ የበጀት ዓመት ከሀምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ዓ.ም ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5፡ ትርጉም

1. **"የበጎ አድራጎት ማህበር"** ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመው **ASSOCIATION FOR PEACE IN ETHIOPIA/ አሶስዬሽን ፎር ፒስ ኢን እትዮጵያ/APE/** ማህበር ነው፡፡
2. **"አዋጅ"** ማለት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ነው፡፡
3. **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የፌደራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የተቋቋመው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ነው፡፡
4. **"ጠቅላላ ጉባኤ"** ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የበጎ አድራጎት ማህበሩ የበላይ አካል ነው፡
5. **"APE"** ማለት ASSOCIATION FOR PEACE IN ETHIOPIA የሚወክል ሲሆን ለሰላም እና ሰላምን ሊያበረታቱ የሚችሉ ጉዳዮች የሚሰራ **የበጎ አድራጎት ማህበር** ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ 6፡ መደበኛ አባላት

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላው ጉባዔ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል፡፡
2. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ/የምታሟላ ማንኛውም/ዋም ኢትዮጵያዊ/ት ሰው መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ትችላለች፡፡

ሀ. በበጎ አድራጎት ማህበሩ አላማና ግብ የሚያምን/የምታምን፤

ለ. እድሜው/ዋ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ/ች፤

ሐ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ የሥነ-ምግባር ደንቦችን የሚቀበል/የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ/የምታደርግ፤

መ. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል/የምትችል

ሠ. በህግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ/ያልተገፈፈች::

## አንቀጽ 7: የክብር አባላት

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል ያልሆኑና የበጎ አድራጎት ማህበሩን አላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፤ የበጎ አድራጎት ማህበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተስማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በበጎ አድራጎት ማህበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ::

2. የክብር አባላት በበጎ አድራጎት ማህበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም::

3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም::

## አንቀጽ 8: የአባላት መብት

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው:
2. የበጎ አድራጎት ማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው::

የበጎ አድራጎት ማህበሩ መደበኛ አባል፡-

ሀ. ለበጎ አድራጎት ማህበሩ ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣

ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለበጎ አድራጎት ማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣

ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለበጎ አድራጎት ማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት፣ እና

መ. አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በስራ አስፈጻሚ ቦርድ የመስማት መብት አለው::

## አንቀጽ 9፡ የአባላት ግዴታ

1. ማንኛውም/ዋም አባል የአባልነት መዋጮን በወቅቱ የመክፈል ፤
2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በፊት የሚፈለግበትን/የሚፈለግባትን ዕዳ የመክፈል ፤
3. ማንኛውም አባል የበጎ አድራጎት ማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሣኔዎችን የማክበር ፤
4. ማንኛውም አባል የበጎ አድራጎት ማህበሩን አላማና የገባቸውን/የገባችውን ግዴታዎች የማክበር፣ የበጎ አድራጎት ማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ፤
5. በበጎ አድራጎት ማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት:

## አንቀጽ 10፡ የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን በጠቅላላ ጉባኤው ይወሰናል፡፡
2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል ሰው በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል/ይጣልባታል፡፡
3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን /የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ/ች አባል ላይ እዳውን/እዳዋን እስኪከፍል/ እስክትከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ የመስጠት ወይም ማንኛውንም ሌላ መብት ሊያነሳ ይችላል:

## አንቀጽ 11፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

አንድ የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል አባልነቱ/ቷ የሚቋረጠው፡-

1. ሲሞት/ስትሞት፣
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
3. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣

4. ለበጎ አድራጎት ማህበሩ ዓላማ መሣካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሣትፎ ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸው በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
5. መዋጮውን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ በጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፣
6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታው/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ/ስትወገድ፣
7. ከበጎ አድራጎት ማህበሩ አባልነት በራሱ/ሷ ፈቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ/ስትጠይቅ ይሆናል፣

## አንቀጽ 12: የበጎ አድራጎት ማህበሩ አደረጃጀት

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ጠቅላላጉባኤ፣ የስራ አመራር ቦርድ፣ሥራአስኪያጅ፣ኦዲተር፣ ሂሳብ ሹም፣ ገንዘብ ያዥና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖረዋል::
2. የበጎ አድራጎት ማህበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው:-




3. የስራ አመራር ቦርድ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ወይም ሥራአስኪያጅ ሆኖ ሊሰራ አይችልም::

## አንቀጽ 13፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና በበጎ አድራጎት ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦
   - ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የበጎ አድራጎት ማህበሩ የበላይ አካል ነው፣
   - ለ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣
   - ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የበጎ አድራጎት ማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ክፍያውን ይወስናል፣
   - መ. የስራ አመራር ቦርድ አባላትን፣ የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሾማል ይሽራል፣
   - ሠ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣
   - ረ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ መፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣
   - ሰ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣
   - ሸ. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣
   - ቀ. በበጎ አድራጎት ማህበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣
   - በ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   - ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣
   - ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣
   - ኀ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣
   - ነ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣
   - ኘ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ከሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውጣኔ ይሠጣል፡፡
   - አ. በበጎ አድራጎት ማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ የበጎ አድራጎት ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል:

2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሠ)፣ (በ)፣ (ቸ) እና (ነ) መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለበጎ አድራጎት ማህበሩ

አመራር አካላት ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 14: የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል:
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው:
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ይኖርባታል:
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል:
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃሣብ ያለው/ያላት የበጎ አድራት ማህበር አባል የልዩነት ሀሣቡን/ቧን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች:
6. ማንኛውም መደበኛ የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የበጎ አድራጎት ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለባለሥልጣን ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች:

## አንቀጽ 15: የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና [illegible] የሚከተለው ነው፣

1. **የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ፣**

   ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች ከጸሀፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

   ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣

   ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣችውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣

መ. ጉባኤው ያጸደቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፤ የሥራና የኦዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣

ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሐፊው/ዋ በአጀንዳነት ያስይዛል/ታስይዛለች፣

2. <u>ምክትል ሰብሳቢ</u>

ሀ. ሰበሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፣

ለ. በሰብሳቢው/ዋ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ሰራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣

3. <u>ፀሐፊ</u>

ሀ. ከሰብሳቢው/ዋ ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉብኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

## አንቀጽ 16: <u>የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ</u>

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሊቀመንበሩ በ60 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ እንደሆን ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከሆነ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የሚሆን/የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፡፡

5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ቀኑን፤ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

6. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

7. በዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡

8. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳነት እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሐፊ/ሊቀመንበር/ፕሬዘዳንት/የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ/ በጽሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡

## አንቀጽ 17: የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. በጎ አድራጎት ማህበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣

2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣

3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወስኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣

4. ጠቅላላ ጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የስራ አመራር አባላትን ለመተካት እንደአስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣

5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዘመን (4 ዓመት) ማረፍ ይኖርባቸዋል፡፡

6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

7. የበጎ አድራጎት ማህበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም።ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱ ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ቀርበው ያልጸደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

## አንቀጽ 18፡ የማህበሩ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የስራ አመራር ቦርድ አባላት ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የበጐ አድራጐት ማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ይሾማል ፣ ይሽራል /ይቀጥራል ፣ ያሰናብታል/፣
2. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ውሣኔዎችንና የሚወጡ እቅዶችን በሥራ አስኪያጁ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
3. የበጎ አድራጎት ማኅበሩን ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የበጎ አድራጐት ማኅበሩ ሥራ አመራር አካል የሚያቀርባቸውን ሀሳቦች ተቀብሎና አስፈላጊም [illegible] የራሱን አስተያየት ጨምሮ ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ለጉባኤው ያቀርባል፣

[illegible] ወይም በማቴሪያል ለበጎ አድራጐት ማኅበሩ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ገቢዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣ ድጋፍ የሚገኝበትንም መንገድ ይቀይሳል፣

5. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች እንደአስፈላጊነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስወስናል፣
6. የበጎ አድራጐት ማኅበሩ የስራ አመራር አካላት የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Authority for Civil Society Organizations

7. የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፤
8. በበጎ አድራጎት ማኅበሩ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት ላይ በመምከር ለጠቅላላው ጉባኤ ለውሣኔ ያቀርባል፤
9. የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤
10. የስራ አመራር ቦርድ አባላት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወጣል፤
11. አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚጠራበት ምክንያት ሲያጋጥም ጥሪ እንዲደረግ ይወስናል፡፡

## አንቀጽ 19: የማህበሩ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

1. የሥራ አመራር ቦርድ 7 አባላት ይኖሩታል፤
2. የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣል፤
3. የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፤

1. ሰብሳቢው/ዋ:-
   - ሀ. የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤
   - ለ. የሥራ አመራር ቦርድ በስብሰባ ያሳለፋቸውን ውሣኔዎች ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባል፤
   - ሐ. የሥራ አመራር ቦርድ የሚያወጣቸውን የበጎ አድራጎት ማኅበሩን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ለጠቅላላው ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል፤
   - መ. ለጠቅላላ ጉባኤውና ለቦርዱ ከተሰጠው ሥልጣን አንፃር ተጠሪነቱ ለጉባኤውና ለቦርዱ ይሆናል፤
   - ሠ. ጠቅላላው ጉባኤና ቦርዱ የሚያሳልፏቸው ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፤
   - ረ. የበጎ አድራጎት ማኅበሩን ማኔጅመንት የሥራ አፈፃፀም በቅርብ ይከታተላል፤
   - ሰ. ጉባኤው ያፀደቀውን የሥራ አፈፃፀምና የኦዲት ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲልክ ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፤
   - ሸ. ከኦዲት ሪፖርት ውጭ ያሉትን ዓመታዊ ሪፖርቶች በጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ያቀርባል፡፡

2. ምክትል ሰብሳቢ፡-

ሀ. ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ ይሠራል፤

ለ. በሰብሳቢው ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ተጨማሪ ሥራ ያከናውናል

3. ፀሐፊ፡-

ሀ. ተጠሪነቱ የሥራ አመራር ቦርድ ነው፤

ለ. የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፤

ሐ. የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤

መ. የሥራ አመራር ቦርድ ጽ/ቤት መዛግብትና ሠነድ ይጠብቃል።

## አንቀጽ 20፡ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የስብሰባ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን

1. የስራ አመራር ቦርድ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በየአስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም በበጎ አድራጐት ማኀበሩ ሥራ አስኪያጅ ሊጠራ ይችላል፣
3. ከየስራ አመራር ቦርድ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል። በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምጽ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሣብ ይፀናል፣
5. የስራ አመራር ቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም አንድ የቦርድ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፣

6. የየስራ አመራር ቦርድ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ሆኖም ለበጎ አድራጎት ማኅበሩ ስራ ለሚወጡት ወጪዎች ማካካሻ ይከፈላል፡፡

## አንቀጽ 21፡ የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለለስራ አመራር ቦርድ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

1. በማናቸውም አካል ዘንድ የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ይወክላል፣ የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ሥራ በተመለከተ ማናቸውም ጉዳዮች ይፈጽማል፣ ውክልና ይሰጣል፣ በበጎ አድራጐት ማኅበሩ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል ውል ይዋዋላል፣

2. በበጎ አድራጎት ማህበሩ ስም የሚከፈተውን የባንክ ሂሣብ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሂሣብ ሹሙ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣

3. በጠቅላላው ጉባኤና በስራ አመራር ቦርድ የሚተላለፉ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

4. የበጎ አድራጎት ማህበሩን የየሶስት ወር እና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶች እያዘጋጀ (በየሶስት ወሩ እና በየዓመቱ) ለቦርዱ ያቀርባል፣

5. የበጎ አድራጐት ማህበሩን ፖሊሲ በማውጣትና የበጀት እና የሥራ እቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣

6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለበጎ አድራጐት ማኅበሩ ገቢ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ስልቶችን በመቀየስ ያስፈጽማል፣

7. የስራ አመራር ቦርድ በሚያወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፣

8. ከሂሣብ ሹሙ እና ከገንዘብ ያዡ የሥራ ኃላፊነቶች ውጭ ያሉትን የሥራ ድልድሎች በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Authority for Civil Society Organizations

9. ሂሣብ ሹምና ገንዘብ ያዥን ጨምሮ፣ በስሩ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተባበረ፣ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የበጎ አድራጎት ማኅበሩን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣

10. የበጎ አድራጎት ማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሌሎች የማኔጅመንት ውሣኔዎችን ይሰጣል፣

11. ሥራ አስኪያጁ የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል ከሆነ ሐሳቡን ለማጽደቅ ወይም በኃላፊነቱ የተከናወነውን ለማጽደቅ በሚያደርገው ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፣

12. የበጎ አድራጎት ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔን በማይቃረን ሁኔታ ከስራ አመራር ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 22: የማህበሩ ሒሣብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሣብ ሹሙ ተጠሪነቱ ለበጎ አድራጎት ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ገቢና ወጪ ሂሣብ ይቆጣጠራል፣ በትክክል እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያደርጋል፣

2. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ሂሣብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሣብ አሠራር ደንብ መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራል፣

3. የበጎ አድራጎት ማህበሩን የባንክ ሂሣብና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሥራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣

4. የበጎ አድራጎት ማህበሩ የሂሣብ መዛግብት እና የተለያዩ ሰነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣

5. የሂሣብ መዝገብ፣ ገቢ እና ወጪ፣ ሀብት እና ዕዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፣

6. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በሚሠማራበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሣብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 23፡ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

ገንዘብ ያዡ ተጠሪነቱ ለበጎ አድራጎት ማህበሩ ሒሳብ ሹም ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፣
2. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል፣ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣
3. ለሥራ ማስኬጃና ለማህበሩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፣
4. ከሂሣብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሂሣብ በየወሩ ያመሳክራል፣
5. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ቼክ ይይዛል፣
6. በጣምራ ፊርማ (በሂሣብ ሹሙ እና በሥራ አስኪያጁ) ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 24፡ የማህበሩ የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ኦዲተር የበጎ አድራጎት ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም የስራ አመራር ቦርድ አባል ሊሆን አይችልም፡፡
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ፤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
   2.1 የበጎ አድራጎት ማህበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣
   2.2 የበጎ አድራጎት ማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
   2.3 በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 25፡ የበጎ አድራጎት ማህበሩ የገቢ ምንጭ

የበጎ አድራጎት ማህበሩ የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ፣ በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 26፡ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ¼ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል።
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ጸሐፊ ወይም ዳይሬክተር የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል።
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ¾ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው።
4. የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያላጸደቀው እንደሆን ባልጸደቀበት ጉዳይ ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይጠራል።
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በባለሥልጣን መ/ቤቱ በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም።

## አንቀጽ 27፡ ስለ በጎ አድራጎት ማህበሩ መዋሃድና መለወጥ

1. በጎ አድራጎት ማህበሩ ወደ ተለያዩ የበጎ አድራት ድርጅቶች የሚከፋፈለው፣ ከሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ ሌላ አይነት በጎ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ¾ኛ ድምፅ ሲወሰን ነው።
2. ከበጎ አድራጎት ማህበሩ ጋር የሚዋሃደው በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና የበጎ አድራጎት ማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ማካተት ይኖርበታል።

## አንቀጽ 28፡ ስለበጎ አድራጎት ማህበሩ መፍረስ

1. በጎ አድራጎት ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ¾ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው በጎ አድራጎት ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የበጎ አድራጎት ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የንብረት ዝርዝር (Inventory) አዘጋጅቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው በጎ አድራጎት ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የበጎ አድራጎት ማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የመንግስት አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 29፡የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

### የመስራች ስምና ፊርማ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|
| 1 | ሽመልስ ፈይሳ ቶላ | |
| 2 | መሪሁን ማንደዬ ማኖ | |
| 3 | ብርሃኑ ቶሎሳ ጋረደው | |
| 4 | ያሬድ አመሃ ሳቀው | |
| 5 | ሀብተማሪያም ለገሰ ሰኚ | |
| 6 | አመለወርቅ ዳምጤ ብሩ | |
| 7 | ሙሉ ጣፋ ሆርዶፋ | |
| 8 | አልማዝ ፈይሳ ቶላ | |
| 9 | ሀይለገብርኤል ደሜ ሆርዶፋ | |
| 10 | አያንቱ በድዬ ሰንበታ | |
| 11 | ሚሮን ስዩም ረጋሳ | |